የምንማፀን ሆነን ልንገኝ ይገባል። ሰላም የክርስትና መታወቂያ አርማ ነውና።

**ብርሃን:-**

“በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃንን አየ፤ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው። ” ኢሳ 9፥2። ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ያህል በዲያብሎስ ቁራኝነት ተይዞ የነበረው አዳም ወደሚደነቀው ብርሃን የተሸጋገረው በክርስቶስ ልደት ነው። እኛም በልደቱ ያገኘነውን የጽድቅ ብርሃን ጠብቀን ለመኖር ብርሃን ወንጌልን ፈጽመን ከኃጢአት ርቀን በጽድቅ ሥራ ተወስነን ብርሃን ሆነን ልንኖር ይገባል።

**ነጻነት:-**

“በነጻነት እንኖር ዘንድ ክርስቶስ ነጻ አወጣን። ከእንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገና በባርነት ቀንበር አትያዙ”። ገላ 5፥1። የሰው ልጅ እግዚአብሔርን በነጻነት እያመሰገነ ይኖር ዘንድ ተፈጥሯልና። ኃጢአት በመሥራት የዲያብሎስ ባርያ ሳንሆን በተሰጠን ነጻነት በመጠቀም የጽድቅ አገልጋዮች ሆነን ልንመላለስ ይገባል።

**ይቅርታ:-**

በአዳም በደል ምክንያት ከአብራኩ የተከፈሉ በሙሉ በደለኛ ሆነው የነበሩበትን ዘመን ለውጦ አዳምንና የልጅ ልጆቹን በደል ደምስሶ ፍቅርን ይመሰርት ዘንድ ጌታ ተወለደ። በምድርና በሰማይ ላሉት ፍቅርን መሠረተ። እርሱ የሰው ልጆችን በደል ሳይቆጥር ሁሉን ይቅር እንዳለ ክርስቲያንም የበደሉትን ሁሉ ይቅር ይል ዘንድ የፈጣሪው ትዕዛዝ ነውና ዘወትር ሊፈጽማት የምትገባ ከእግዚአብሔር ጸጋ የምታስደምር የልደቱን ብርሃን ለማየት እንደበቁ በዚህም ደስ እንደተሰኙ እንደ ቅዱሳን መላእክት ለእውነተኛ ምስጋና የምታደርስ



የጽድቅ መሠረት የበረከት በር ናት። ማቴ 18፥21-23፤ ማቴ 5፥23-25። መባህን ትተህ ሂድ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ የሚለው አምላካዊ ቃል ይቅርታ የክርስትና ሕይወት መመሪያ መሆኑን ያሳያልና ዘወትር ልንፈጽማት ይገባል።

**ፍቅር:-**

ፍቅር ሰሃቦ ለወልድ ኃያል እም መንበሩ ወአብጽሖ እስከለሞት /ፍቅር ኃያል ወልድን ከዙፋኑ አወረደው እስከ ሞትም አደረሰው።/ ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደተናገረው እግዚአብሔር አምላክ የሰው ልጅን በደል ሳይቆጥር በዙፋኑ ሆኖ ምሬሃለሁ ማለት ሲችል ፍቅሩን ይገልጽ ዘንድ በከብቶች በረት ተወለደ። እውነተኛ ፍቅሩ ለክርስትናችን መሠረት ለጽድቃችን ፋና እንደሆነ መጻሕፍት ያረጋግጣሉ።

እንግዲህ በልደቱ ያገኘነውን ሰላም፣ ነጻነት፣ ይቅርታ፣ ብርሃንና ፍቅር ዋጋ የተከፈለበት ጸጋ የወረስንበት በመሆኑ ዘወትር በድንቅ ፍቅሩ የሚታደገን አምላካችን እግዚአብሔር በሰጠን ጸጋ እስከ መጨረሻው ድረስ ጸንተን እንድንኖር ክብራችንንና ጸጋችንን አስተውለን ከኃጢአት ርቀን በንስሐ ታጥበን እራሳችንን ለክርስቶስ የተወደደ መስዋዕት አድርገን እንድናቀርብ የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት የቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነት አይለየን። አሜን።

**በኢ/ኦ/ተ/ቤ/በሰ/ት/ቤቶች ማ/መምሪያ**
**ማኅበረ ቅዱሳን**
**የአሜሪካ ማዕከል ትምህርትና ሥልጠና ክፍል**
**ታህሳስ 2002 ዓ.ም.**



**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ**
**አሐዱ አምላክ አሜን።**

# ብርሃን ልደቱ ለመድኃኔዓለም

## የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት ተወለደ

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን የስሙ ቀዳሽ የርስቱ ወራሽ ይሆን ዘንድ ከምድር አፈር አበጅቶ የሕይወት እስትንፋስ እፍ ብሎበት በአርአያውና በአምሳሉ በዕለተ ዓርብ ፈጠረው። ዘፍ 1፥26-28። በፀጋ የከበረ ሆኖ ፈጣሪውን እያገለገለ የተፈጠረበትን ዓላማ ለ7 ዓመት በመጠበቅ እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘ በክብር ኖረ። ዘፍ2፥7። ዳሩ ግን በሰባተኛው ዓመት በሰይጣን ምክር አማካኝነት የተሰጠውን ሕግ አፍርሶ ዕፀ በለስን በላ፤ በዚህም ምክንያት ከክብሩ ተዋርዶ ከገነት ተባሮ በምድረ ፋይድ ተጣለ። ዘፍ 2፥16-17 ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ ተፈረደበት። ዘፍ 3፥ 1-17። ባህርይው ጉስቆለ፤ አዳምና ሔዋን የዲያብሎስ አገልጋይ ሆኑ። በእንዲህ ያለ ጽኑ ፍርድ ውስጥ እያሉ አዳም ስለበደሉ አዘነ፤ አለቀሰ፤ ፈጣሪውንም ይቅርታ ጠየቀ። የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም በፈጠረው ፍጥረት ሳይጨክን ”ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ“ የሚል የምሕረት ተስፋ ሰጠው። አዳምም ተስፋውን እየጠበቀ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ያህል ምህረትን ሲናፍቅ ኖረ። ዘፍ 3፥16።

## *ቀጠሮው ሲደርስ ምን ሆነ?*

የተናገረውን የማያስቀር የምህረት አምላክ አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ለአዳም አባታችን የገባውን ቃል ለመፈጸም ትንቢቱ ሲደርስ ምሳሌው ሲፈጸም ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ እግዘአብሔር ከሴት (ከድንግል) የተወለደውን አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ላከው" ገላ 4፥4 ዘፍ 3፥22 እንዳለው ለመዳናችን ምክንያት ከቅድስት ድንግል ማርያም መድኃኔዓለም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በቤተልሔም በከብቶች በረት ተወለደ። ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅም "ድንግል ፈጣሪዋን ወለደች እርሱም የፈጠረውን ሥጋ ተዋሐደ " ሲል በሃይማኖተ አበው እንደገለፀው። ማቴ 1፥19--22 ፤ኢሳ 7፥14፤ መዝ 2፥7

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር ታህሳስ 29 ቀን በዕለተ ማክሰኞ በድንግልና ተጸንሶ በኅቱም ድንግልና ተወለደ። ኢሳ 7፥14፤ ማቴ 1፥1-23፤ ሉቃ 2፥18።

## *በተወለደ ጊዜ ምን ተፈጸመ?*

አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም በከብቶች በረት በተወለደ ጊዜ እንስሳት/ ትንፋሻቸውን ገብረውለታል። ሰብዐ ሰገልም ወርቁን ለመንግሥቱ፣ ዕጣኑን ለክህነቱ፣ ከርቤውን ለሞቱ እንዲሆን እጅ መንሻ አድርገው ገብረውለታል። የተናቁ ኖሎት የመልአኩን የምሥራች ቃል ሰምተው በአዲስ ምስጋና አመስግነውታል። ግሩማን ቅዱሳን መላእክትም በላይ በአርያም በዙፋኑ በፍጹም ክብሩ አይተውት "በምድር ሥምረቱ ለሰብእ" ብለው ተቀኝተዋል። ታላቁ የቤተክርስቲያን ሊቅ ቅዱስ



አትናቴዎስም እንዲህ ብሏል። "አምላክ ሰው ሰው አምላክ የሆነበት ይህ ምስጢር ፍሬ ተዋሕዶ በእውነት እፁብ ድንቅ ነው ማናቸውን አስቤ ላድንቅ መለኮታዊ ባህርይ ባለመመርመር ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብሎ በመመስገን ከባሕርይ አባትህ አብ ጋር በቅድምና መኖርህን ላድንቅን? ወይስ በአምሳለ ሕጻን ተገልጸህ በግእዘ ሕፃናት ሆነህ በእናትህ እቅፍ መያዝክን" እያለ የወልድን ከድንግል መወለድ ገልጾታል።

ለወልድ ሁለት ልደት እንዳለው በቀዳማዊዉ ልደቱ ዘመን እንደማይቆጠርለት በደኃራዊ ልደቱም በምስጢር ቤተልሔም ኤፍራታ ተብላ ከምትታወቀው ድንግል ማርያም እንዲወለድና ዘመን እንደማይቆጠርለት ነቢዩ ሚኪያስ እንዲህ ሲል መስክሯል። "አንቺ ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ አንቺ በይሁዳ አዕላፋት ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ግን አውጣጡ/ልደቱ/ ከቀድሞ ጀምሮ ለዘላለም የሆነ ለእስራኤልም ገዢ የሚሆን ይመጣልኛል" (ይወለድልናል) ሚኪ 5፥2 ። ከድንግል የተወለደው ህፃኑ አማኑኤል በልደቱ ፋና ጨለማን አርቆ ብርሃንን ያወጣ የጽድቅ ፀሐይ፣ የብርሃን መገኛ፣ የሰላም ባለቤት ነው። ቃልም ሥጋና ነፍስን ተዋሕዶ የተገለጸው በዳግም ልደት ነው። ቅድመ ዓለም ያለ እናት ተወልዷል። ሰው ሆኖ የተገለጸው /ወልድ ዘበላዕሉ/ ይባላል። የአብ አንድያ ልጁ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ወልድ ዋሕድ ነውና በደኃራዊ ልደቱ ከድንግል ያለ አባት ተወልዷል። ከድንግል በመወለዱ ዘመን ይቆጠርለታል። ሕፃን ዘበታህቱ የሚባለውም ለዚህ ነው። ኢሳይያስ ነቢይም "ህፃን ተወልደ ለነ ወልድ ተውህበ ለነ" ሲል ገልጾታል። "ሕፃን



ተወልዶልናልና፥ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል" እንዲል። ኢሳ 2÷9። ይኸም ወልድ በፀጋ ለሰውና ለመላእክት አባታቸው መሆኑን ይገልፃል። በመለኮቱ ዘመን የማይቆጠርለት በመሆኑ ዘላለማዊ አባት ተብሏል። ዘላለማዊ እርሱ ዘመን ስለሚቆጠርለትም ህፃን ተብሏል። በመዝሙረ ዳዊት እግዚአብሔር አብ ወልድን ቅድመ ዓለም እንደወለደው ሲያጠይቅ "ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ" ይላል መዝ 109፥3። ወልድም ከፍጥረት በፊት ከዘላለም ጀምሮ ከአብ መወለዱን ሲገልጽ "ተራሮች ገና ሳይመሰረቱ ከኮረብቶች በፊት እኔ ተወለድሁ" ይላል። ምሳ 8፥25።

## *ከልደቱ ያገኘነው ምንድን ነው?*

### ዳግም ልደት፡-

በአዳም በደል ምክንያት አጥተነው የነበረው ልጅነታችንን ክርስቶስ በልደቱ ዳግመኛ እንደመለሰልን ነባቤ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ "ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" ዮሐ 1፥12 በማለት ገልጾታል።

### ሰላም፡-

በጌታችን ልደት ለዓለም ሁሉ የሚሆን ዘላለማዊ ሰላም ተገኝቷል። ይህም "ክብር ለእግዚአብሔር በሰማያት ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጐ ፈቃድ" እያሉ ቅዱሳን መላእክት በመዘመራቸው ተረጋግጧል። ሉቃ 2፥14። ስለዚህ በክርስቶስ ያገኘነው እውነተኛ ሰላም በእኛ ጸንቶ እንዲኖር ዘወትር በጾምና በጸሎት እየተጋን ስለሰላም